# ከአቶ ስብሓት ነጋ ያልተመለሱ ጥያቄዎች

*ይኩኖ መስፍን /ቦስተን/*

ባለፉት ሳምንታት አቶ ስብሓት ነጋ የህወሓት መስራች አባልና የኢህአዴግ ከፍተኛ አመራር አባል ለተለያዩ በሰሜን አመሪካ ለሚገኙ የኢትዮጵያ የራድዮ ፕሮግራም ስርጭቶች ሰፋ ያለ ቃለ መጠይቅ ሲሰጡ ሰንብተዋል:: እነዚህ ቃለ መጠይቆች ያተኮሩት በወቅታዊው የአገራችን የፖሊቲካ ሁኔታ ማለትም አብዮታዊ ዴሞክራሲና የኢትዮጵያ ህገ መንግስት፣ በኤርትራና ኤርትራውያን ላይ ኢህአዴግ የሚከተለው ፖሊሲ፣ ስለ ዴሞክራሲ፣ ሰብአዊ መብትና ምርጫ እንዲሁም ኢህአዴግ ስላከናወናቸው ስራዎችና እድሜያቸው የገፋ የአመራር አባላት በጥሮታ መልክ ከስልጣን መልቀቅን ጉዳይ በጥቂቱ የሚጠቀሱ ናቸው::

አቶ ስብሓት ነጋ በህወሓት መስራችነታቸውና አንጋፋ ታጋይ በመሆናቸው በተደረገው ቃለ መጠይቅ የሰጡት ምላሽ በርከት ያሉ ኢትዮጵያውያን በጥሞና ተከታትለውታል:: በዚሁ መሰረትም በዙ አስተያቶች በተለያዩ ድረገፆች አቶ ስብሓት በመደገፍም ሆነ በመቃወም ተሰንዝረው ለንባብ በቅተዋል:: ምክንያቱም እየተነሱ ያሉ ጥያቄዎች ወቅታዊና መሰረታዊ ያገራችን የወደፊት እድል የሚወስኑ በመሆናቸው ማንኛውም ዜጋ በዚህ ጉዳይ ላይ ሃሳቡን የመግለፅና የመከራከር ሃላፊነት ስላለው ነው:: ባጠቃላይ ኢህአዴግ የሚከተለው የፖለቲካ አቅጣጫ የመደገፍና የመቃወም መብት የማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜግነታዊ ሃላፊነት እንጂ አንዱ ሲወድ የሚሰጠው ሲጠላ የሚነሳው ችሮታ ስላልሆነ ነው::

አቶ ስብሓት ነጋ በሰጡት ቃለመጠይቅ ዙርያ የጥያቄው አቀራረብና አያያዝ ካልሆነ በስተቀር ይዘታው ከሞላ ጎደል ተመሳሳይ ነበር ማለት ይቻላል:: የአመሪካ ድምፅ ራድዮ አዘጋጅ ጠንከር ያለ መጠየቅ የሚገባቸውን ጥያቄዎች በማቅረብ ውይይቱ ሰፋ እንዲልና ፋይዳ እንዲኖረው አድረጓል:: ስለሆነም እነዚህ በርካታ የሚድያ ውጤቶች በየ ድረገፃቸው የአቶ ስብሓት ውይይት ይዘው ቀርበዋል:: እኛም የሁሉንም አዳመጥን:: አነበብንም:: እንግድያውስ በተሰጠው መልስ ሁሉም ባይሆኑ ጥቂትና ዋና ዋናዎችን ያልተስማማሁባቸውና ቀደም ብለው አቶ ስብሓት ራሳቸው ካሉት የማይጣጣም መስሎ ስለታየኝ በዚሁ ጉዳይ የግሌን አስተያየት ለመሰንዘር እንደሚከተለው አጠር ባለመልኩ አቀርበዋለሁ::

ኢህአዴግ በኤርትራ ላይ የሚከተለው ፖሊሲ በሚመለከት በተለይ በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ሳብያ ለአገሪቱ የፀጥታ አደጋ ናቸው ተብሎ የታመነባቸው ኤርትራውያን ከኢትዮጵያ እንዲወጡ ተደርጓል:: በቅርቡ የሚንስትሮች ምክርቤት ደግሞ እነዚህ ኤርትራውያን ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለሱና ንብረታቸው እንዲያስተዳድሩ ብቻ ሳይሆን እንደ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ እንዲኖሩና ኢንቨስት እንዲያደርጉ አዲስ ህግ ወጥተዋል:: ይህንን ለምን ሆነ? የንብረት መመለስ ጉዳይ ከተነሳ አይቀር የኢትዮጵያውያን በኤርትራ ውስጥ የነበረውን ንብረትስ ምን ይሁን? የሚል ጥያቄ ነበር የቀረበው::

"አቶ ስብሓት ሲመልሱ: ሰዎቹ ከኢትዮጵያ እንዲወጡ መደረጉ ትክክለኛ ነበር:: አሁን ሰዎቹ ተመልሰው ንብረታቸው እንዲያስተዳድሩ ማድረጋችን ግን መጀመርያ ኢህአዴግ ዴሞክራሲያዊ ባህሪው ነው:: ሁለተኛ የመብት ጉዳይ ነው:: ሶስተኛ በዚያን ሰአት የነበረ ስጋት አሁን የለም::የኢትዮጵያውያን ንብረት የመመለስ ጉዳይ

## ከአቶ ስብሓት ነጋ ያልተመለሱ ጥያቄዎች

*ይኩኖ መስፍን /ቦስተን/*

በፍርድ ቤት አልቋል እሱን እንጠብቃለን ነው ያሉን:: አያይዘውም መንግስት አንዳችም የኤርትራውያን ንብረት እንዳልያዘ ገልፀዋል"::

የሚገርመው አቶ ስብሓት ከኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት በፊት የኤርትራውያን በኢትዮጵያ ውስጥ የነበራቸው የፈለጉትን የማድረግ መብት አቶ ስብሓት ብቻቸው የሚያውቁት መስሎዋቸው ይሆን? በጣም በርካታ ኤርትራውያን በተደራጀም ሆነ በግል ቁጥር ስፍር የሌለው የኢትዮጵያ ገንዘብ ከባንኮቻችን እየተበደሩ ከትንሹ እስከ አሉ የሚባሉ የንግድ፣ የባንክና የተለያዩ ሸቀጦች በመስራት ከፍተኛ ገንዘብ ወደ ሃገራቸው እንዳጓጓዙና እንዳካበቱ መንግስት ቀደም በሎ ገልጿል::

ይህ ገንዘብ የህዝብ ሃብት ነው:: መንግስት ይህን የማስመለስ ሃላፊነት የለውም ማለት ነው አቶ ስብሓት? የነዚህ አይነት ሰዎች ንብረት በአገራችን ውስጥ የለም ነው የሚሉን? እሳቸው ይህን ጠንቅቀው ያውቁታል:: የእድሜ ባለፀጋና ባለሰፊ ተሞክሮ እንደመሆንዎ መጠን በሰል ያለ አስተያየትና ላገር የሚጠቅም ሃሳብ ከመስጠት ይልቅ ለራስዎ ፖለቲካ ጥቅም የሚያገለግል ቃላት መደርደር ትርፉ ትእዝብት ብቻ ነው የሚሆነው:: ለድምፂ ወያነ ራድዮ በሰጡት ቃለመጠይቅ መሰረት የተናገሩት አንድ አካራካሪ ጉዳይ ነበር:: እሱም ህወሓት የኤርትራን ሉአላዊነት ሊደፍር ነው:: በቅርቡም ሊወረን እየተዘጋጀ ነው ብሎ ሻእቢያ ያወራል እና እንዴት ነው ተብለው ሲጠየቁ: እኛ ለኤርትራ ነፃነት ከሻዕቢያ በላይ ጠንክረን ቆመናል:: ሻዕቢያ ከደርግ ጋር የእርቅ ድርድር ሲያደርግ እኛ በፍፁም መሆን እንደሌለበት ጠንካራ አቋም ወስደን በኤርትራ ያለንን አመለካከት አመስክረናል:: እሱ ብቻ ሳይሆን አሁን ዛሬ ኤርትራ ብትወረር በአመራር ላይ ያለው ሃይል እኔ እሰከማውቀው እጅና እግሮ አስሮ ቀጭ አይልም ብለው ነበር:: ሳምንቱ ደግሞ እኛ ነፃነት አልሰጠናቸውም:: በራሳቸው ነው ነፃ የወጡት ብለዋል:: ግን ለምን አቶ ስብሓት እንደ ኢትዮጵያ መንግስት ባለስልጣን መጀመርያ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ነው መሆን ያለበት:: ኤርትራ እና ኤርትራውያን የራሳቸው አገር እና መንግስት አላቸው:: ስርአታቸውም የራሳቸው:: ድንበራችን ሲጥሱ እንደማንኛውም አገር እንደ አገር መልስ መስጠት ነው:: እንደ አገር:: መንግስታቸው ዜጎቻችን ሲበድልና ሲገድል አንድም ሰው ቢሆን እስከ መጨረሻ ለወገናችን መቆም እየተገባ እርስዎና ጓደኞችዎ ግን በተገላቢጦሽ ሆነ ለምን?

"ኢህአዴግ ዴሞክራሲያዊ ባህሪው ሰለሆነ ነው ይህን አዲስ ህግ ያወጣነው"::

በኢትዮጵያ የዴሞክራሲ ግንባታ ሂደት መሰረታዊ የዴሞክራሳዊ ጥያቄዎች በሚነሱበት ግዜ ኢህአዴግ የሚላቸው ገና በሂደት ነው ያለነው:: ጀማሪዎች ነን:: አመሪካኖች ሁለት መቶ አመት ፈጀባቸው እኛ ደግሞ እየተጓዝን ነን ይሉናል:: ባገር ውስጥ በጣም ብዙ ወሳኝ የሆኑ እልባት ያላገኙ አበይት ጉዳዮች አሉ:: ኢህአዴግ ያልመለሳቸው:: የፍትህ አካላት ነፃ የማድረግ፣ ተቃዋሚውም መንግስትም የሚቀበለው ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ የማቋቋም ጉዳይ፣ ነፃ ምርጫ ማካሄድ፣ የፕሬስ ነፃነት በሰፊው እየተገደበ ሰለመሆኑ እና ፍትሃዊ የሆነ የሚድያ አጠቃቀም ጥያቄ ገና አልተመለሰም:: በኢህአዴግ እጅ ውስጥ ያለ የአንድ ግንባር የፖለቲካ ፕሮፓጋንዳ ሲደግም የሚውል ሚድያ ነው ያለን:: አልያም ራሳችን ከአለም መጨረሻ ከሆኑት ከሻዕቢያና ሞቶ ከተቀበረ ደርግ ጋር የምናወዳድር ከሆነ

# ከአቶ ስብሓት ነጋ ያልተመለሱ ጥያቄዎች

*ይኩኖ መስፍን /ቦስተን/*

ትርጉሙ ወደነሱ እየወረድን ነው ማለት ነው:: ስለዚህ አቶ ስብሓት ከምን ተነስተው ነው የኢህአዴግ ባህሪ መገለጫው ዴሞክራሲያዊ ነው የሚሉን?

የኢህአዴግ ዴሞክራሲያዊ ባህሪ እና የህዝብ መብት የመጠበቅ ጉዳይ ከተነሳ በ1969 ዓ/ም ህወሓት ገና በረሃ እያለ አቶ ስብሓት ነጋ ሊቀ መንበር እያሉ ማለት ነው:: ፊውዳል፣ ሃብታም ገበሬ፣ ኢድዩ ባጠቃላይ ፀረ ህወሓት ወይም ከህወሓት ጋር መሰረታዊ ልዩነት አላቸው ተብለው የተጠረጠሩ ዜጎች ቤት ንብረታቸው እንዲወረሱ ተደርገዋል:: የሚገርመው ምውረሳቸው አይደለም:: በግዜው የነበረ ስሜት ሊሆን ይችላል:: ኢህአዴግ በትረ ስልጣኑ ከጨበጠ በኋላ ትግራይ ውስጥ የክልል ተወካዮች ምክርቤት ተሰይሟል:: ጠቅላላ የህወሓት አባላትና ደጋፊ ነው ምክር ቤቱ:: እና በ1969 ዓ/ም ህወሓት የወሰደው እርምጃ ህግ እንዲሆን ተቀብለን አፅድቀናል ማለቱ ነው:: እስከ ዛሬ እለት ከተለያየ የስደት ቦታዎች ተመልሰው ቤቶቻቸው መግባት ያልቻሉ ኢትዮጵያውያን በጣም ብዙ ናቸው:: በተለይ በትግራይ ክልል:: አንድ ምሳሌ ልጥቀስ፡ ለኢትዮጵያ በቁርጠኝነትና ብእምነት በጠቅላይ ሚንስትርነት፣ የአዲስ አበባ ከንቲባ፣ በተባበሩት መንግስታት ቋሚ የኢትዮጵያ ተወካይ የነበሩ ነፍሰሄር ክቡር ደጃዝማች ዶክተር ዘውዴ ገበረስላሴ እስከ እለተ ሞታቸው በጥገኝነት እንዲኖሩ ተደርጓል:: የሂወታቸው መጨረሻም ሆነ:: ይሄ ነው የኢህአዴግ ዴሞክራሲያዊ ባህሪ:: አቶ ስብሓት ይህን ደግሞ በግልም በደምብ የሚያውቁት የሚያሳዝን ታሪክ ነው::

*"አሁን ስጋቱ የለም"*

ስጋቱ ወይም አደጋው አሁን በከፋ መልኩ አለ ባይ ነኝ:: በጦርነቱ ግዜ የተፈራው ስጋት ሳይደርስ ችግር ይፈጥራሉ የተባሉት ኤርትራውያን ወደ አገራቸው ተሸኝተዋል:: ምስጋና ለተለያዩ የኢትዮጵያ የፀጥታ ባለሞያዎች:: ከጦርነቱ በኋላ ሻዕብያ ኢትዮጵያን ለማዳከምና ብሎም ለመበታተን ሌተቀን እየሰራ ነው:: የራሱ ነፃ አውጪ ድርጅቶች እየፈለፈለ ነው:: ሰራዊቱ እና ኮማንዶዎቹ ኢትዮጵያ ውስጥ ሰርገው እየገቡ ሽበራ እየፈጠሩ ነው:: መልእክተኞቹ መንገድ ላይ ፈንጅ እየቀበሩ ህዝባችን እና ንብረታችን እያወደሙ ነው:: በኦጋዴን ሶማሌ፣ በአፋር፣ በሁመራ፣ በአድያቦ ተደጋጋሚ አፈናዎችና ግድያዎች እየተፈፀሙ ነው:: በአዲስ አበባ በቅርቡ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት አመታዊ ስብሰባ በታወቀ የሻዕብያ ኮለኔል የሚመራ የሽብር ቡዱን ከፍተኛ ሽብር ለመፍጠር ሲሞክሩ ያዝናቸው በሎ የኢትዮጵያ መንግስት መግለጫ ሰጥቷል:: የተያዙት ሰዎች እና ፈንጆቻቸውም በቴለቪዥን አሳይተውናል:: በቅርቡ ኢትዮጵያውያን በስፋት እያነጋገረ ያለው የጉንበት ሰባት ቡዱንም የሻዕብያ እጅ አለበት እየተባለ ነው:: ስለዚ ስጋቱ ለምን የለም አቶ ስብሓት? ሻዕብያ ኢትዮጵያውያንንለመጥፎ ተግባር መላክ ከቻለ (የምትነግሩን ሀቅ ከሆነ ማለት ነው?) የራሱ ዜጎች መላክና ማዘዝ አይችልም ብለው ለማመን መነሻዎት ምን ይሆን? ወይስ ቤተ መንግስት አደጋ ካልደረሰ ስጋት የለም ማለት ነው?

*"የመብት ጉዳይ ነው"*

## ከአቶ ስብሓት ነጋ ያልተመለሱ ጥያቄዎች

*ይኩኖ መስፍን /ቦስተን/*

የመብት ጉዳይ ሲባል የኢትዮጵያውያን የመብት ጉዳይስ ለምንድነው ችላ ተብሎ የሚታለፍው:: በኤርትራ ውስጥ ይኖሩ የነበሩ ኢትዮጵያውያን ጥረው ግረው ያገኙት ሃብት ሻዕብያ ዘርፎና እነሱን አሰቃይቶ ባዶ እጃቸው እንዲባረሩ አድርጓል:: አገራቸው ገብተውም በተለያዩ የግዚያዊ መጠለያ ስፍራዎች ለአመታት እስከ ቅርብ ግዜ ይሰቃዩ እንደነበሩ በተደጋጋሚ ጉዳዩ የሚመለከታቸውና ነገሩን ያሳዘናቸው ግለሰቦችና ድርጅቶች ሲገልፁ ቆይተዋል:: በዚህ ጉዳይ ላይ በግዜው የኢህአዴግ መልስም ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ያሳዘነ እንደነበር ራሱ ኢህአዴግ አይክደውም:: ጦርነቱ ሲቀሰቀስም ሻዕብያ ንፅሃን ኢትዮጵያውያን ባልዋሉበት ኢትዮጵያውያን በመሆናቸው ብቻ በኮንተይነር ውስጥ አቃጥሎ ፈጅቶዋቸዋል:: በሂወት አገራቸው መድረስ ያልቻሉት በሺዎች ናቸው:: ስለ ንብረትና ገንዘብ ማውራት ሌላ ነገር ነው:: በሻዕብያ ግፈኛ አሰራርና በኢህአዴግ ቸለልተኝነት::

### አብዮታዊ ዴሞክራሲና የኢትዮጵያ ህገመንግስት

ኢህአዴግ ህገመንግስቱን አከብራለሁ ይላል:: ግን ደግሞ አብዮታዊ ዴሞክራሲ መመሪያየ ነው በሎ ኢትዮጵያ ለረዥም አመታት ካልመራ የሚፈለገው እድገትና ልማት እንደማይመጣ እየነገረን ነው:: እና ከህገመንግስቱ ማለትም የመድብለ ፓርቲ ስርአት ጋር አይጋጭም ወይ?

"አቶ ስብሓት ይህ የኛ ፍላጎት እና አቅጣጫ ነው:: የፈለገ ሰው የራሱ አካሄድ እና ፕላን ይኖረዋል:: ስላዚህ ሌሎችም የሚፈልጉትን የማስፈርና የመንቀሳቀስ መብቱ አላቸው ነው የሚሉት"::

መሰረታዊው ጉዳይ ኢህአዴግ ልክ እንደሌሎች ተፎካካሪ ድርጅት ነው ወይ ነው ዋናው ጥያቄ:: ኢህአዴግ እላይ የተጠቀሱት የዲሞክራሲ ምሶሶ የሆኑ የአገር የስቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ብቻውን በተቆጣጠረበት ግዜ እና ደግሞ ለረዥም አመታት የመምራት ፍላጎት ይጋጫል ብቻ ሳይሆን ፀረ ዲሞክራሲ ነው:: የአገራችን ልማት እና ዲሞክራሲ የሚገነቡት መተማመን ሰፍኖ ነፃና ግልፅ በሆነ መንገድ ሁሉም ለሰላም፣ ለፍትህ እና ዲሞክራሲ ሲሰራ ብቻ ነው እነዚህ ነገሮች የሚሟሉት:: ኢህአዴግ ለአምሳ አመት ስለገዛ ችግራችን አይቀረፍም:: ነፃ ሆኖ የመደራጀት፣ የመንቀሳቀስ እና የመወዳደር ስርአት ሲኖርና ኢህአዴግ ከተሸነፈ እንኳ እናሳ የመንግስት አካል ሆኖ አገሩ ውስጥ በሰላም ሲኖርና ተመልሶ በሰላማዊ ውድድር፣ በዴሞክራሲያዊ ምርጫ ስልጣን ሲቆጣጠር ነው ዲሞክራሲ ገነባሁ ማለት የሚገባው::

በመጨረሻ አቶ ስብሓት የቀረበላቸው ጥያቄ ለኢትዮጵያ ህዝብ በደልነው የምትሉት ነገር ካለ?

"ቀደም ብለው የነበሩን ችግሮች በግዜ አለመፍታታችን ነው:: ለምሳሌ የአንጃው ችግር ቀደም ብሎ መፈታት ነበረበት:: አስር አመት አልሰራንም በዚህ ለኢትዮጵያ ህዝብ በድለነዋል"::

# <u>ከአቶ ስብሓት ነጋ ያልተመለሱ ጥያቄዎች</u>

*ይኩኖ መስፍን /ቦስተን/*

ስለዚህ ተሰራ ተብሎ የተዘረዘረው ሁሉ በላፈው ስምንት አመት ብቻ ነው የተሰራው ማለት ነው? 30 ዩኒቨረሲቲ ሰርተናል ብለው የለም:: የመንገድ፣ የመብራት፣ ንፁህ ውሃ፣ ትምህርት እና ሌሎች አንጃው አልነበረበትም እያሉን ነው? በኔ እምነት ታሪክ ታሪክ ነው:: አንድ ሰው ብቻውን የሚያውቀው ሚስጥር አይደለም:: አንጃዎቹ በድሉም በስህተቱም አብረዎት ነበሩ:: ታሪክ የመሰረዝ ተግባራቹህ የመጀመርያው አይደለም:: በቅርቡ ህዳሴ በሚል ስያሜ ተዘጋጅቶ በመላው አለም በኢህአዴግ የተበተነ ቪድዮ የሚያሳየው ከደርግ ጋር የተደረገው ፊልሚያ አሁን አቶ መለስን በሚደግፉ የጦር አዛገሮች አመራር ልድል እንዳበቁ ያሳያል:: ምን አይነት ባህልና ታሪክ ለሚቀጥለው ትውልድ ማስተላለፍ እንደሚፈለግ ግራ የሚያጋባ ነው:: ባለፈው አመት በኮሌኔል ተወልደ ገበረተንሳይ የተፃፈ "ባድመ እንደ ምክንያት" የሚል መፅሃፍ አንብቤ እርሶ እዚህ ካሉት ጋር ይመሳሰላል:: ኮሌኔሉ የመከላከያ የመረጃ ክፍል ሃላፊ ነበርኩ ይላል:: ጦርነቱ ተጀምሮ እስኪያልቅ ድረስም ግንባር ነበርኩ ብኋል:: የመፅሃፉ ዋነኛ መልእክት ጦርነቱ በድል የተጠናቀቀው በአቶ መለስ የሰከነ አመራርና በአቶ ፀጋይ በርሀ የሚልሻ መሪነት ነው በሎናል:: ሰራዊቱን ለድል ያበቁ ወታደራዊ ጠበብት ስምና ተግባር መጽሃፉ ውስጥ አልተጠቀሰም:: ባለፈው ሳምንት አቶ መለስ ለፋይናንሻል ታይምስ (Financial Times) በሰጡት ቃለ መጠይቅ መሰረት እሳቸው ከኤርትራ ጋር በተደረገው ጦርነት በፍፁም እንዳልተስማሙና እንደማይደግፉት ግልፅ አድረገዋል:: የአብላጫው ድምፅ ተቀብለው እንደሰሩ አስምረውበታል ጠቅላይ ሚንስተር መለስ:: ኮለኔሉ ምን ይሉ ይሆን? አቶ ስብሓት ለትውልድ የሚተርፍ ቅንነት ሃቅ ነግራቹህን እኛም ብንማርበት ከጉዳቱ ጥቅሙ ይበልጥ ነበር:: ግለሰቦቹን ስለጠሉ አልነበሩም፣ ፋይዳ የላቸውም እኛ ብቻ ነን ሓቀኛ በሎ ለግል ፖለቲካ ታሪክ ማጣመም ወይም መሰረዝ በተለይ ከእርሶ የማንጠብቀው ነው:: አለኝ የሚሉት ዴሞክራሲያዊ ባህሪ ብቻቸውን የሚያምኑትና የግል እምነት ብቻ ሆኖ ይቀራል::

ለማጠቃለል ኢትዮጵያ የምትለማውና የምታድገው ሁሉም ኢትዮጵያዊ በአንድነትና ፍቅር ለሰላም፣ ለፍትህና ለዲሞክረሲ ተሳታፊ የሚሆንበትን መንገድ ማበጀት ይጠበቅብናል::ችግሮቻችን በውይይትና በሰላም ከፈታናቸው ልማታችን ይፋጠናል:: ይህን አምነን ወደፊት የሚወስደንን ጎዳና አብረን እንገንባ:: አንድ ግለሰብ፣ አንድ ፓርቲ ወይም ግንባር ብቻውን የትም መድረስ እንደማይችል አውቀን በደልን ይቅር ይቅር ተባብለን ህዝባችንን በጋራ እንታደግ:: በተቀሩት ያልተነሱ ጉዳዮች ሗላ እመለስባቸዋለህ ለዛሬ በዚህ ይብቃኝ::

ቸር ይግጠመን

እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይጠብቅ!